# “እግዚአብሔር ያሳየዎ: ክርስቶስ ያመልክተዎ!”

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

nigatuasteraye@gmail.com

ጥቅምት ፳፻፺ ዓ.ም.

እግዚአብሔር በሚያሳየው ክርስቶስ በሚያመለክተው መስመር የማይሰለፍ፤ በቡድንና በጥቅም በተራቆተ ስሜት ተሳስሮና ተለባብሶ የሚኖር ህብረተሰብ፤ ከራሱ በሚፈልቅ ስሜት ወይም ከውጭ በሚመጣ ግፊት ከመጠፋፋት ቢያመልጥም፤ ከመለያየት ማምለጥ ፈጽሞ አይችልም። ክርስቶስም “እርስ በርስዋ የምትለያይ አገር ሁሉ ትጠፋለች። እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማ ወይም ቤት አይቆምም” (ማቴ 12፡5) በማለት አስጠንቅቋል። ፍረዱብን እያሉ ተቆራኝተው ሰሞኑን ወደኛ በቀረቡት በማህበረ ቅዱሳንና በአባማትያስበአባማትያስ መካከል የተከሰተው ይህ ነው።

አይታችሁ ፍረዱብን በማለት በዚህ መልክ ወደኛ ከቀረቡ፤ ርትዕ ፍትህ፤ በጥቅም፤ በቡድን፤ በጎሳና በቂም እንዳትመዘን፤ አባቶቻችን “እግዚአብሔር ያሳየዎ ክርስቶስ ያመልክተዎ” በሚለው ቅዱስ ባህላቸው ጥያቄያቸውን ተቀብለን እንድንፈርድ ሃላፊነቱ በኛ ትከሻ ላይ ወድቋል። አንተም ተው አንተም ተው በሚለው ኢትዮጵያዊ መንገድ ሁለቱም በሸፍጥ የተጓዙባቸውን መንገዶች ለይተን በማሳየት ሁሉቱም እንዲመለሱ ገስጸን እንዲስተካከሉ ከማድረግ ይልቅ፤ በጠየመና በተግደመደመ መንፈስ የምንናገረውና እየጻፍን የምንበትነው ራስን ከትዝብት ላይ ከመጣል በቀር አይጠቅመንምና እናቁም።

የምንሰነዝረው ትችትና ፍርድ፤ በስንዴ መካከል የበቀለ አረም፤ ስሩ ከስንዴው ስር ጋራ በመቆላለፉ አረሙን ለመንቀል ሲታሰብ፤ ስንዴውም አብሮ እንዳይነቀልና ጥንቃቄ እንዲደረግ ክርስቶስ ያሳየንን መንገድ መከተል ይገባናል። ስህተት የሰሩትን ሰዎች ደብቆ፤ ስህተቱን ብቻ መናገር፤ ነፋስ በመጎሰም ድርጅቱን መናድና በድርጅቱ የታቀፉትን የዋህን ወገኖች አብሮ መጉዳት ስለሆነ ተገቢ አይደለም። በዚህ ፈታኝ ወቅት የጥንት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን እውነትን ለማግኘት የተጠቀሙበትን መንገድ መከተሉ አማራጭ የሌለው የሚጠቅም ይመስለኛል።

ከኔ በእድሜ ከፍ ያላችሁና እኩል የሆናችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ እንደምታስታውሱት፤ ጥንታውያን አባቶቻችን ከዘመነ ኦሪት በፊት ሀልወተ እግዚአብሔርን ከማወቅ ደረጃ ላይ ሳይደርሱ፤ ይህን የመሰሉ ጉዳዮች ሲገጥሟቸው ፍርድን ረብ በሌላቸው ነገሮች በተሰበረ ሚዛን እንዳያዘቡ “አንተ ታቦት ፍረድ” በማለት ላላወቁት ኃይል አደራ ይሉ ነበር።

የፍርድን ቅድስና ለመጠበቅ አባቶቻችን በየደረሱበት ዘመን ደረጃ በደራጃ የተጠቀሙባቸውን መንገዶች በጥንቃቄና በማስተዋል ብንመከታቸውና ልንጠቀምባቸው ብንሞክር፤ ዛሬ ከፊታችን የተደቀኑብንን ችግሮች ለመፍታት ባልከበደን ነበር።

ከላይ እንዳልኩት፤ ቅድመ ኦሪት “አንተ ተራራ፡ አንተ አባይ፡ አንተ ሰማይ ፍረድ” ይሉ ነበር። በዘመነ ኦሪት “አንተ ታቦት፤ አንተ አግዚአብሔር ፍረድ” ይሉ ነበር። በዘመነ ሥጋዌ ደግሞ “ክርስቶስ ያመልክተዎ” የሚለውን አከሉበት። በዘመነ ደርግ ባባቶች የተተኩ ሰዎች ያባቶችን ለቀው፤ ፍርድን በአብዮት እይታና በፓርቲ ምልከታ ሰይፍ ላይ መሰረቷት። *[ኢትዮጵያ ስለአለፈችባቸው ሕግጋቶች ዝርዝሩን ለማንበብ ከፈለጉ የሚቀጥለውን ሰንሰለት ይጫኑ፡፡* ኢትዮጵያ ያለፈችባቸው ሕግጋቶች ]

“እግዚአብሔር ባሳየዎ ክርስቶስ ባማለከተዎ” የሚለውን ጠብቀን ማስጠበቅ የሚገባን ካህናት፤ በተለይም በወያኔ እየተካኑ የገቡ ቀሳውስት ጳጳሳት መነኮሳት፤ የዘመኑ ሰባኪዎችና ሚናቸውን የሳቱ ቆሞሳት ቤተ መቅደሱ ወደ ንግድ ቤትነት፤ ቅዳሴው ወደ

ገንዘብ ማትረፊያነት፤ አውደ ምህረቱ ወደ ማስታወቂያ ሰሌዳነት ቀየሩት። ቀድሼ፤ ዘምሬና ሰብኬ የማገኘው ገቢ አይቅርብኝ እንጅ፤ ገዳማት ቢፈርሱ፤ ምእመናን ቢፈልሱ፤ ድንበሮች ቢቃወሱ የፖለቲካ ሥራ ስለሆነ ምን አናገረን የሚሉ ሆነዋል። "ጋቢየን አጣፍቼ መቋሚየን ተደግፌ ልማዳዊ ድጋሜን ካደረስኩ በቤተ ክርስቲያን በአገር ላይ ለሚደርሰው ችግር ምን አገባን" የሚሉ ምእመናንም ተከሰተዋል። የህሊና ዳኝነታችንን፤ የመንፈስ ምስክርነታችንና፤ የአዕምሮ አስተያየታችን አዛብተን፤ እውነትን አጠይመን፤ የሸፍጠኛውን ሰው ስም ደብቀን ነፋስ ጎሳሚዎች ሆነናል። እነ Democritus ከተናገሩት ከእግዚአብሔር አልባነት ግንዛቤ በታች እጅግ በጣም ተንኮታኩተን ወድቀናል።

Democritus የተባለውን ሰው ጠቅሻለሁና፤ Christopher Hitchens የተባሉ ሰው Democritus የተናገረውን ሙሉ ሀሳቡን ብጠቅሰው የኢትዮጵያዊነት መሰመራችንን ምን ያህል እንደ ሳትን ለማሳየት የሚረዳ ይመስለኛል። Christopher Hitchens የሚባሉ ሰው "god is not great" በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፋቸው ከዘመነ ልደት 500 አመት አካባቢ የነበረውን Democritus የተባለውን ሰው በመጥቀስ እንዲህ አሉ። "Religion comes from the period of human prehistory where nobody –not even the mighty Democritus who concluded that all matter was made from atoms- had the smallest idea what was going on. It comes from the bawling and fearful infancy of our species, and is a babyish attempt to meet our inescapable demand for knowledge (as well as for comfort, reassurance, and other infantile needs). Today the least educated of my children knows much more about natural order than any of the founders of religion, and one would like to think –thought the connection is not s fully demonstrable one- that is why they seem to uninterested in sending fellow humans to hell."(64) <u>በትክክል ማስቀመጥ ከቻልኩ ሀሳቡ እንደሚከተለው ነው።</u>

ዴማክርተስ የተባሉ ሰው "ፍጥረታት ሁሉ ከአተሞች ተሰሩ ብለው ከመደምደማቸው በፊት ሃይማኖት ነበረ። ሃይማኖት ሰው በፍርሀት ተውጦ ከሚያላዝንና ካልበሰለ ጭንቅላት በሚጨነቅበት ጊዜ የመነጨ ነው። ሰው ለምቾቱና ለህይወቱ የተረጋገጠ ዋስትና ለማግኘት ከሚያደርገው ተፈጥሯዊ ዳሰሳ ማምለጥ ከማይችለው ጭንቅላት የፈለቀ ነው። ዛሬ ግን ከልጆቼ መካከል የመጨረሻው ተማሪ፤ ሃማኖትን ከጀመሩት አባቶች ይልቅ ስለ ተፈጥሮ ብዙ ያውቃል። <u>የስነ ፍጥረት ግንኙነት ሙሉ በሙሉ አልተገለጸም ብሎ ስለሚያስብም፤ በሰው ላይ ፈርዶ ወደ ገሀንም ከመላክ ይቆጠባል።</u>" አሉ።

ይህን ሀሳብ የጠቀስኩት የኛ የኢትዮጵያውያን እምነትና ሀሳብ፤ ሰው ከሙሉ እውቀት ላይ በመድረስ፤ በእግዚአብሔር አመራር ላይ ያለውን እምነትና እውቀት ይተካል። የእግዚአብሔር ምሪትም አያስፈልገውም ከሚለው ሀሳብ ጋራ ቢቃረንም፤ በመሳሳታችን የሚፈርድብን ህቡዕ ኃይል አለ ብለው ሳያምኑ፤ ሙሉ በሙሉ በማያውቁት ነገር በሰው ላይ ከመፍረድ <u>ይቆጠባሉ። በህቡዕ የሚመለከተን ፈራጅ አምላክ አለን የምንል አማኞች፤ የተሰራውን ጥፋት ለማረምና ሰሪውን ለመገሰጽ መነሻና መድረሻ የምናደርገው በሥጋ ዝምድና፤ በመንደር ልጅነትና በቡድን ግፊት ላይ በተመሰረተ ሀሳብና ስሜት ነው። በመሳሳታችን የሚፈርድብን ህቡዕ ኃይል አለ ብለው የማያምኑ ሰዎች ለፍርድ የሚሰጡትን ጥንቃቄ፤ በህቡዕ የሚመለከተን ፈራጅ አምላክ አለን ብለን የምናምን ሰዎች ለፍርድ ከምንሰጠው ጥንቃቄ ጋራ ሳንጻጽረው፤ የኛ ያማኞች በተለይም የካህናት ትችት ነቀፋና ድጋፍ በጥቅም በጎሳና በቡድን ላይ በመመስረቱ ያለንበትን ዘመን እጅግ የከፋ አድርጎ አሳይቶኛል።</u>

ከዚህ ልዕለ አዕምሮ ርቀን እጅግ በከፋው፤ "ለእመ ሀልቀ ሰብእ ሡዑ ሰብአ" ማለትም፡- <u>"የምትሰዋው እንስሳ ካጣህ ሰው ሰዋ"</u> ከሚለው ከወያኔ ህግ ላይ ወደቅን። ውድቀታችንን ለማሳየት ከዚህ በታች በዘረዘርኳቸው አንቀጾች ይህችን ጦማር አቀርባለሁ።

<u>፩ኛ</u>፡- አንተ ታቦት ፍረድ ወይም እግዚአብሔር ያሳየዎ፡
<u>፪ኛ</u>፡- ክርስቶስ ያመልከተዎ (ዮሐ ፰፡፯)
<u>፫ኛ</u>፡- አቡነ ማትያስ እና ማኅበረ ቅዱሳን

ሀ. አቡነ ማትያስ ለቤተ ክርስቲያን ያተረፉት ጥቅምና ጉዳት

ለ. የአቡነ ማትያስ በቤተ ክርድቲያናችን ላይ ያሳዩት ብርታትና ድካም።

<u>፬ኛ</u>፡- አቡነ ማትያስ ለቤተ ክርስቲያን ያተረፉት ጥቅምና ጉዳት፤ ወይም ብርታትና ድካም።

<u>፭ ኛ</u>፡- የማህበረ ቅዱሳን አባላት በአገር ውስጥና በውጭ የፈጸሚቸው በጎና ከፉ ነገሮች
ሀ. በአገር ውስጥ

ለ. በአሜሪካ

፯ ኛ:- መደምደሚያ

## ፩ኛ:- "አንተ ታቦት ፍረድ ! ወይም እግዚአብሔር ያሳየዎ"

ኢትዮጵያውያን "አንተ ታቦት ፍረድ ! ወይም እግዚአብሔር ያሳየዎ" እያሉ በፍርድ ወንበር ላይ ለተቀመጠ ዳኛ ወይም ሸንጎ ይሰጡት የነበረው ማስጠንቀቂያ ከየት መጣ? ፍርድ እንዳይዛባ ይህ ማስጠንቀቂያ፤ "በህዝብ ላይ ለመፍረድ መልካሙንና ክፉውን ይለይ ዘንድ፤ ለባርያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው። አለዚያማ በዚህ ታላቅ ሕዝብ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል? ብሎ ከተናገረው ከሰሎሞን ጥበብ የተወሰደ እንደሆነ ሊቃውንት አበው ይናገራሉ። የህዝቡን ታላቅነት መረዳቱ፤ የመፍረድ አቅሙን ማወቁ፤ የጥበብ ምንጭ የሆነውን እግዚአብሄርን መጠየቁና ህሊናውን በህዝብ ልዕልናና በህቡዕ በሚፈርደው ፈጣሪ ላይ መመሰረቱ ሰሎሞንን ታላቅ የጥበብ ሰው አደረገው። ሰሎሞን ህዝቡን ከፍ! ራሱን ዝቅ! በማድረግ መልካሙንና ክፉውን የመለየትና የመፍረድ ችሎታ እንዲያገኝ ተመኘ። የሰሎሞን ምኞት ጠላቱን ለመጉዳት ወዳጁን ለመጥቀም ወይም የራሱን ስሜት ለማርካት ረኀም እድሜና ኃይል አልነበረም። በዚህ ተምኔቱ "ፍርድን ትለይ ዘንድ ማስተዋልን ለመንህ እንጅ ለራስህ ዕድሜና ሀብት ወይም የጠላትን መውደቅ ሳትለምን ጥበብ ለምነሀልና እንደቃልህ አድርጌልሀለሁ" (ቀ.ነ.ም. ፫፡፱) የሚል አምላካዊ ቃለ ሢመት ተሰማው። ለሚዛናዊ ፍርድ ከሚያፈልቀው ህቡእ አምላክም የከሃሊነትን ልዕለ አእምሮ ተቀዳጀ።

መንፈሱን ስሜቱን በዚህ ልዕለ አዕምሮ እየቃኘ፤ የመጀመሪያውን ፍርድ ያፈለቀው፤ በዝሙት እየተዳደሩ ባንድ ቤት የሚኖሩ ሴቶች ላይ ያሳለፈው የፍርድ ውሳኔ ነበር። ባንድ ቤት የሚኖሩ ሁለቱም ሴቶች ባንድ ወቅት ወለዱ። የናትነት ሀላፊነት የጎደላት አንደኛዋ ልጇን ተጭና ገደለችው። በንዝህላልነት ተጭና የገደለችውን ልጇን በጓደኛዋ ጎን አስተኝታ፤ ያልሞተው የጓደኛዋን ልጅ ወሰደችባት። ልጇን ከመነጠቋ በተጨማሪ ሙት እንድትታቀፍ የተደረገችው እናት ስትነቃ በጎኗ ያገኘችው ልጅ የሷ ያልሆነና ያውም የሞተ እንደሆነ ተረዳች። ያልሞተውን ልጇን በጓደኛዋ እቅፍ አየችው። "ሬሳሽን ወስጅ፡ በሕይወት እያለ የታቀፍሽውን ልጄን መልሽ" ብላ በቁጣና በብስጭ ተነሳች።

ሁለቱም ተካሰው ከሰሎሞን ቀረቡ። ሰሎሞን ከሁለቱ ባላንጣወች በቀር ፍርዱን የሚመሰረትበት የሰው ምስክር አላገኘም። የነበረው ምርጫ የራሱን ጥበብ መጠቀም ነበር። የተጠቀመው ተጨባጭ የሆነውን ሰይፍ ነበርና አምጡልኝ ብሎ አዘዘ። "ልጁን በሰይፍ ከሁለት ከፍላችሁ ለሚከራከሩት እናቶች አካፍሏቸው " ብሎ ወሰነ። ያልወለደችው እናት "ለእኔም ላንችም አይሰጥም። ንጉሥ ሰሎሞን እንደፈረደው ከሁለት ይከፈልና ድርሻችንን እንካፈል" አለች። የወለደች እናት የልጇን ግማሽ አካል መታቀፍ ይቅርና ይሰንጠቅ የሚልውን የሰሎሞንን ፍርድ ገሰሰችው። ያልወለደችው እናት እውነትን ከተደበቀችበት ፈልፍሎ ለማውጣት ሰሎሞን የተጠቀመበትን "ይሰንጠቅ" የሚለውን ደግፋ ቆመች ። ሰሎሞን በሰይፉ አማካይነት እውነት ሰንጥቃ ስትወጣ ተመለከተና "በህይወት እንዳለ ለሷ ስጧት እንጅ አይሰንጠቅ " ብላ ለጮኸችው ልጁ ይሰጥ ብሎ ችሎቱን ዘጋ። ( ፫፡፳፯)

ያልወለደች እናት ለሁለት ተሰንጥቆ ይካፈሉት ብሎ ሰሎሞን መፈተሻ አድርጎ ካቀረበው ሀሳብ ጋራ ተስማማ። እንደወርቅ ከማትዝገው እውነትና ከእናትነት ስሜት አፈነገጠ። "በህይወት እንዳለ ለሷ ስጧት እንጅ አይገደል" ብላ የጮኸች እናት እንደ ወርቅ ከማትዝገው ፍትህ እና ከናትናት ስሜት ጋራ ተገናዘበለት። ከዚያ በኋላ ሰሎሞን " ለሁለት ሳይከፈል በህይወት እንዳለ ለሷ ስጧት" ላለችው እናት ፈረደ። (፳፪)። ሰይፏ እንደ ወርቅ ለማትዝገው ፍትህ፡ ሰም ነበረች። <u>የመጽሐፍ ትርጓሜ ሊቃውንት መምህሮቻችን እውነት የባለ ሥልጣንን ቃል የመግሰስ ኃይል እንዳላት በቅኔያቸው ዘረፉ አስተምረውናል።</u>

በቅዳሴያችን ወደ እግዚአብሄር በምንቀርብባት እለት "ተውህቦ ልቡና ለዳዊት ወጥበብ ለሶሎሞን" (ቅ ገ ቁ ፳፪) እያልን የማንጎራጎር ልምድ ለማድረስ ወይም በሩቅ እያየን የሰሎሞንን ጥበብ እንድናደንቅ ብቻ አልነበረም። ዘመኑ ሲከፋ ለማስረጃና ለምስክር የሚጠቀስ ሰው ይጠፋል። በዚህ ጊዜ በየቀኗ ህሊና ፈታኞች የሆኑ ነገሮች መከሰታቸው አይቀርም። በዚህ ግዜ ምን አገባኝ ብለን እንዳንሸሽ፤ በጥቅም እውነትን እንዳንገስ፤ ማንም ባለ ሥልጣን በስልጣኑ ተንተርሶ የሚዋሸውን በመቃወም "በህዝብ ላይ ለመፍረድ መልካሙንና ክፉውን ይለይ ዘንድ፤ ለባርያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው። አለዚያማ በዚህ ታላቅ ሕዝብ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል? እንድንል ነበር። "ፍርድን ትለይ ዘንድ ማስተዋልን ለመንህ እንጅ ለራስህ ዕድሜና ሀብት ወይም የጠላትን መውደቅ ሳትለምን ጥበብ ለምነሀልና እንደቃልህ አድርጌልሀለሁ" የሚለውን መለኮታዊ መልስ በማግኘት ልክ እንደ ሰሎሞን እንድንፈርድ ነበር። ዛሬ ግን ማስረጃዎች በፊታችን ተደርድረው ሳሉ፤ ሰይፍም ሳያስፈልገን፤ <u>"እግዚአብሔር ያሳየዎ"</u> የሚለውን ረሳነው። "ክርስቶስ ያመልክተዎ" የሚለውንም እንዳለመሰልጠን አድርገን ወሰድነው። "ለእመ ሀልቀ ሰብእ ሡዑ ሰብአ" ማለትም፡- "የምትሰዋው እንስሳ ካጣህ ሰው ሰዋ" ከሚለው የሰውን ሥጋ ለመስዋዕትነት አጥብቆ ከሚሻው ከወያኔ ህግና እምነት ላይ ወደቅን።

## ፪ኛ:-ክርስቶስ ያመልክተዎ (ዮሐ ፳:፲)

በክርስትና እምነትና ትምህርት "እውነቱን እውነት ሀሰቱን ሀሰት" በማለት ላይ ንግግራችንን ሀሳባችንን እንድንመሰረት ክርስቶስ አመልክቶን ነበር። በክርስትና እምነት እውነትን አጠይሞ የተሳሳተውን ሰውሮ መናገር ስህተት ነው። የክርስትና መጨረሻው መጽሐፍ ክርስቶስ ልብንና ሀሳብን የሚመረምር ነው (ራዕ ፪:፳፫) ብሎ ይጀምርና፤ "ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን የሚከፍል" ብሎም ይደመድማል (ምዕ ፳፪:፲፪)። ክርስቶስ ልብንና ሀሳብን የሚመረምርና ለሁሉም እንደየስራው የሚፈርድ ነው። ቅዱስ ጳውሎስም "ሁሉም የየራሱን ሸክም ይሸከም" ብሏል።

ዮሐንስ የሚባለው የእስክንድርያው ኦርቶዶክሳዊው ሊቅ ክርስቲያናዊውን ነገረ መለኮት ተንትኖ ያስረደባትን አንቀጽ የደመደመው "ወንሕነሰ ኩልነ እለ ብነ ልብ ክርስቶሳዊ ዘበአማን ኢንሔሊ ተቃርኖተ ጽድቅ" ማለትም:- (ሃ, 90; 38 ) ብሎ ነው። ይህም "በእውነት ክርስቶሳዊ ልብ አለን የምንል ከሆነ፤ እውነትን በማገዳምደምና አጠይሞ በመናገር መኖርን እናቁም" ማለት ነው። ወላጆቻችንም "እውነት ተናግሮ ከመሸበት ማደር" እያሉ በመናገር ያሳደጉን፤ እየዋሸን እየቀጠፍን ከግፈኞች ጋራ በደስታና በሀሴት ከምንኖረው ኑሮ ይልቅ፤ እውነት እየተናገርን በጨለማ ቤት ከታሰሩት ጋር መታሰርን እንድንመርጥ የሚያሳየን ነው። "ቀንና ሌሊት ይፈራረቃሉ ለእውነት ግን ተፈራራቂ የላትምና አትልቀቃት" ይሉንም ነበር።

አንዱን አንዱ ተጭኖ ሲገለው ሁላችንም እያየን ነው። ዳኞችም ምስክሮች እኛው ነን። እግዚአብሔር ያዝልቅላቸውና ማህበረ ቅዱሳንና አቡነ ማትያስ እኛኑ በዳኝነት ሰይመው ፍረዱ እያሉን ነው። አልሰማንም አላየንም እንዳንል የሚካሰሱባቸውን ነገሮች ሁለቱም አቅርበውልናል። ሰሎሞን"በህዝብ ላይ ለመፍረድ መልካሙንና መልካም ያልሆኑ ውን ይለይ ዘንድ፤ ለባርያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው። አለዚያማ በዚህ ታላቅ ሕዝብ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል? እንዳለው፤ እያንዳንዳችን ከራሳችን ጀምሮ ለሰባዊ ህዝብነታችን ልዕልና ሰጥተን የቀረቡትን ነገሮች እግዚአብሄር በሚያሰየን ራእይና፤ ክርስቶስ "እውነት ነጻ ታወጣችኋለች" ብሎ ባመለከተን ምልክት ከተመራን ያባ ማትያስ ክስ ከማንና ለምን እንደመነጨች ማየት እንችላለን። የማህበር ቅዱሳንን ስህተት እንድናስተካክልም ትረዳናለች። በራሳችን ምስክርነትና ዳኝነት ወጣቱን ትውልድ ተጭኖ ለመግደል የተዘጋጀው ወያኔ ፓትርያርክ አርጎ በሰየማቸው ሰው እየፈተነን ነው። ከግል ቂም፤ ከጎሳና ረብ ከሌለው ቡድን ራሳችንን አርቀን "እንደየ ስራው እንደ የግብሩ በግልጽ ሳታዳሉ ፍረዱ" ከሚለው መለኮታዊ ቃል ጋራ ሳንጋጭ፤ ብንችል በህገ ክርስቶስ፤ ባንችል በህገ ኦሪት ለመፍረድ ይረዳን ዘንድ እራሴ የተረዳሁትን የአቡነ ማትያስንና የማህበረ ቅዱሳንን ደካማና ጠንካራ ጎኖቻቸውን ከዚህ በታች አቀርባለሁ።

## ፫ኛ:-አቡነ ማትያስ እና ማኅበረ ቅዱሳን

በአቡነ ማትያስና በማህበረ ቅዱሳን መካከል የተከሰተው ውዝግብ፤ ወያኔዎች ሲያጠራቅሙት ኖረው፤ አሁን ራሳቸው ወያኔዎች ደባቸውን ለመፈጸም በሚረዳቸው መንገድ ያፈነዱት ውዝግብ ነው። ይህን የመሳሰሉትን ውዝግቦችም ሆኑ ስለነገረ መለኮት መዛባት የተማርነውንና የምናውቀውን ስንናገር አንድ ጊዜ መናፍቃን ናቸው፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ገለልተኞች ናቸው የሚል ስም በመስጠት ሁለቱም ሲዘምቱብን መኖራቸው እራሳቸውም የሚከዱት አይደለም።

ከዚህ ቀደም ደጋግሜ እንደገለጽኩት፤ አንድን የቤተ ክርስቲያን አባል ከተጠመቀባት፤ ካመነባትና ካደገባት ቤተ ክርስቲያን ገለልተኛ የሚያደርገው፤ እነሱ በሚያወሩት አሉባልታ ሳይሆን፤ ራሱ ግለ ሰቡ እምነቱን አልቀበልም ብሎ ሲተወው፤ ሃይማኖቱን ጥሶ እንግዳ ትምህርት ይዞ በመነሳቱ በሊቃውንቱና በተመሳሳይ አብያተ ክርስቲያናት ተመዝኖ ወድቆ ሲገኝ፤ የሚሰጠውን ምክር አልቀበልም ሲል፤ ወይም ለግል ጥቅሙ ቤተ ክርስቲያኒቱን ተገን አድርጎ በሞራል ውድቀት ተከሶ ሲረጋገጥበት፤ ለምእመናን እንቅፋት እንዳይሆን ሲባል ሲወሰንበት ብቻ ነው።

"የገብያ ግርግር ለቀጣፊ በጀው" እንዲሉ፤ የሲኖዶሱን መከፋፈል እንደ እድል በመጠቀም፤ አንዳንድ የዘመኑ ሰባኪዎች፤ የማህበረ ቅዱሳን መሪዎችን ነን የሚሉ ሰዎችና በቅርቡ በህዝብና በካህናት ህብረት እንደተወገዘው ግለሰብ ገልልተኛ ነኝ እያለ በውንብድና መኖር በጣም የሚያሳዝንና በትእግስት የማይታለፍ ስህተት ነው። ከሁሉም የሚብሰው፤ በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን በመካሄድ ላይ የሚታየውን የመሰለ ስህተት ነው። ያካባቢው ህዝብ ስህተቱን በማስረጃ ለአቡነ ማትያስ ካቀረበላቸው በኋላ፤ ከራሳቸው ካባ ማትያስ ምንም ነገር ሳይሰማ የቤተ ክህነቱን ጋዜጣ መደበቂያና ማወናበጃ ሆኖ መቅረቡ፤ በቅድስት ቤተ ክርስቲያችን ላይ በመካሄድ ያለውን በደል እጽፍ ድርብ አድርጎ አቅርቦታል። በዚህ ጉዳይ ላይ ወደፊት በሰፊው እንሄድበታለን።

እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች በቤተ ክርስቲያናችን ሲፈጠሩ ማንም አማኝ እግዚአብሔር ከሚያሰየው ክርስቶስ ከሚያመለክተው ስሜቱን ሳያርቅ፤ አቅሙ የፈቀደለትን ከማድርግ መገለል ተገቢ አይደለም። በበኩሌ ደጋግሜ እንደገለጽኩት ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ

ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ገለልተኛ አይደለሁም። ገለልተኛ ነኝ ብየ ባምን ኖሮ፤ አቡነ ማትያስ የውስጧን ቤተ ክርስቲያን እወክላለሁ በሚሉበት ጊዜ፤ የማህበረ ቅዱሳን ወኪሎች ያቃወሱትን ትምህርትና እምነት አስተካክለው የጎበጠውን አቃንተው እንዲመለሱ በከንሳስ ምእመናን በተጋበዙ ጊዜ ከመስማማት ይልቅ እንዳይመጡ ብየ መቃወም እችል ነበር።

ነገር ግን በነገረ መለኮት መቃወስና ባስተዳደር መዛባት ራሴን ከነሱ ማራቄና ከቤተ ክህነቱ ደመዎዝ መቀበያ ስም ዝርዝር ከታጸፈበት መዝገብ ውስጥ ስሜ ባለመኖሩ ገለልተኛ ነህ ሊያሰኘኝ አይችልም። <u>ከሊቃውንት መምህሮቼ እንደተማርኩት የቤተ ክርስቲያን ልጅነቴን የማረጋግጠው ነገረ መለኮቱ ጠብቄ ለማስጠበቅ ባለኝ ጽናት እንጅ በወር ደመወዝ አይደለም።</u> በእኔም ሆነ በተመሳሳይ መስመር ላይ ባሉት የቤተ ክርስቲያኒቱ ሰዎች ላይ ገለልተኞች ናቸው እያሉ ማስወራት፤ ምስክርነትን ለማዳፈን በእውነት ላይ የሚደረግ የሸፍጥ ዘመቻ ነውና በቤተ ክርስቲያናችን ህግ የሚያስወግዝ ሥርየት የሌለው በደል ነው። <u>አቡነ ማትያስና ጥቂት የማኀበረ ቅዱሳን መሪዎች ነን የሚሉ ሰዎች በመተባበር ይህን በደል ሲፈጽሙ ቆይተዋል። ይህም ስህተት ሁለቱንም ያስጠይቃቸዋል።</u>

ሆኑም አቡነ ማትያስ በቤተ ክርስቲያናችን መመሪያ ሲለኩ፤ እንኳን ለፓትርያርክነት ለነበሩበት ቦታ የበቁ አይደሉም ማለትና፤ በተሳሳተ መንገድ በመጌዝ ላይ ያሉት እንደነ ከፈለኝ ያሉ ጥቂት የማህበረ ቅዱሳን መሪዎች ከተሳሳቱበት መንገድ ይመለሱ በማለት ድምጼን ከማሰማት በቀር ገለልተኛ ነኝ ብየም አላውቅም።

ምንም እንኳ የማህበረ ቅዱሳን መሪዎች ነን የሚሉ እንደነ ዳንዔል ክብረትና ከፈለኝን የመሳሰሉ ሰዎች በሩቅና በቅርብ የፈጸሙት ደባ ቢበዛም፤ ነገረ መለኮቱን ቢያዛቡም፤ እኔን ቢጎዱኝም፤ ባገር ውስጥ ያሉ የማህበረ ቅዱሳን ልጆች፤ ለምወዳት ላሳደገችኝ ላስተማረችኝ ቤተ ክርስቲያኔ የሰሩላትን እኔ አልሰራሁላትምና፤ በዚህ አከብራቸዋለሁ። አመሰግናቼዋለሁም።

በተረፈ፤ የማህበረ ቅዱሳን ወኪል በመሆን ከፈለኝ ወልደ ጊዮርጊስና፤ በከንሳስ ከተማ እምነቱን ካቃወሰና ህዝቡን ከፋፈለ በኋላ፤ ዲያቆን ነኝ በማለት በከንሳስ ኪዳነ ምህረት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተደበቀው ወንድ ወሰን የተባለው ግለ ሰብ፤ ከቤተ መቅደስ እንዲገለሉ፤ **በየቦታውም ለፈጸሙት ስህተት** እንዲጸጸቱ፤ መገሰጽ እንጅ እነዚህን የመሳሰሉ ሰርጎ ገቦች በፈጸሙት ስህተት ድርጅቱ ይፍረስ፤ የሰበሰቡት ገንዘቡ ይወረስ ማለት፤ ወያኔን መደገፍና ቤተ ክርስቲያንን ማዳከም ይሆናል ብየ እገምታለሁ። እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነቴ ለሁሉም በሚጠቀም መንገድ ለመቋጨት ይቻል ዘንድ ያባ ማትያስንና የማህበረ ቅዱሳንን ጉዳትና ጥቅም ደካማና ብርቱ ጎን በማነጻጸር ለማቅረብ ተገደድኩ። ከዚህ በታች በማቀርበው ከተሳሳትኩ አርሙኝ እያልኩ ንጽጽሬን ከአቡነ ማትያስ እጀምራለሁ።

## ፩ኛ:- <u>አቡነ ማትያስ ለቤተ ክርስቲያን ያተረፉት ጥቅምና ጉዳት፤ ወይም ብርታትና ድካም።</u>

### ሀ. <u>አቡነ ማትያስ በቤተ ክርስቲያናችን ባሰለፉት ህይወታቸው የሚታወቁበት ምንድነው?</u>

አቡነ ማትያስ ለቤተ ክርስቲያን ሰሯቸው አደረጌቸው የሚባሉት ምንኩስና፤ አቡነ ቀሲስነት፤ ጵጵስና እና ፓትርያርክነት ናቸው። በእነሱም ያለፉት በሚቃረን መንገድ መሆኑን ለማሳየት፤ በየአረፍተ ነገሮች መጨረሻ ባሰምርኩባቸው ቃላት ላይ ያተኩሩ።

፩ኛ:- መጻህፍተ መነኮሳቱን ሳይማሩ ሳይረዱ "በልጅነቴ መነኮስኩ" ይላሉ፤ <u>ምኑን አውቀው?</u>

፪ኛ:- በአቡነ ቀሲስነት አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ለመረዳት የበቁናቸው ተብለው በእውቀታቸው ባመክሯቸውና በሰባዊ ባህርያቸው ተመርጠው የተሰየሙትን አባ በትረ የሚባሉትን፤ የተሐድሶ ጊዜአዊ ጉባዔ መሪ የነበሩት ዶክተር ክነፈርግብ ዘለቀ አባረው፤ ያላንዳች ታዛቢ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን መሳሪያ ለማድረግ በማሰብ፤ በዚያን ጊዜ አባ ተክለ ማርያም አሳራትን (የዛሬው የወያኔ ፓትርያክ) ማለት ነው። አቡነ ቀሲስ ሆነው አቡነ ተክለ ሃይማኖትን እንዲረዱ አደረጌቸው። <u>ለጥፋት መሳሪያነት</u>

፫ኛ:- በነ ንቡረዕድ ድሜጥሮስና በዶክተር አባ ሀብተ ሥላሴ (አቡነ ጢሞቴዎስ) ተጽእኖ ጳጳስ ሆኑ፤ <u>በአማላጅ</u>

፬ኛ:- በነ አቶ ስብሀት ነጋ አቀነባባሪነት ፓትርያርክ ነኝ አሉ። <u>በምቱርነት</u>

አቡነ ማትያስ ከመሾማቸው በፊት የቤተክርስያኗን አንደነት ለማምጣት እጅግ መልካም አጋጣሚ ነበር። በወቅቱ የገጠማቸውን ዝርዝሩ ለማንበብ ከፈለጉ የሚቀጥሉትን ሁለት ሰንሰለቶች ይጫኑ።

- *ዝርዝሩን ለማንበብ ከፈለጉ የሚቀጥለውን ሰንሰለት ይጫኑ፡፡* <u>"ጭንጋፍ (ምቱር) ፓትርያርክ"</u>
- *ዝርዝሩን ለማንበብ ከፈለጉ የሚቀጥለውን ሰንሰለት ይጫኑ፡፡* <u>አቡነ ማትያስ : "እንዲህ ያለ ፓትርያርክ አይተን አናውቅም"</u>

አቡነ ማትያስ ከ፤ እስከ 4 የመጡባቸውን እርከኖች ስናጠቃልላቸው፤ ያለ እውቀት፤ ለመሳሪያናት ፤ ባማላጅና በምቱርነት የተጓዙባቸው እንጅ፤ ገብቷቸው በችሎታቸውና በብቃታቸው የመጡባቸው አለመሆናቸውን ከማሳየት በቀር በበጎ ጎን የሚገልጿቸው አይደሉም።

## ለ. <u>የአቡነ ማትያስ ብርታትና ድካም።</u>

አቡነ ቀሲስ አባ ተክለ ማርያም፤ በቤተ ክህነት ግቢ ባንድ ቤት አብረን በቆየንባቸው ጊዜዎች፤ <u>የዋህ፤ ደግ፤ ርህሩህ፤ ገራ ገርና ሰው ወዳጅ እንደነበሩ አውቃለሁ።</u> ይህ የማውቅላቸው <u>ብርታታቸው</u> ነው። በሰው ምክርም ሆነ አውቀውም ሳያውቁም እራሳቸው የፈጸሟቸው ከዚህ በታች የገለጿካቸውን <u>ስህተቶቻቸውን </u>አውቃለሁ።

፩ኛ፡- ካድሬ ሆነው ከባህታዊ ቀለመወርቅ ካሳሁን ጋራ መልካም መንግሥት ነው እያሉ በጎንደር ከተማ የሰበኩለትን ደርግን ካዱ።

፪ኛ፡- ቤተ ክርስቲያን አምና የሰጠቻቸውን የኢየሩሳሌምን ገዳም ከደው ተሰደድኩ ብለው እንግሊዝ አገር ገቡ።

፫ኛ፡- የሾሟቸውን ፓትርያርክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ካዱ።

፬ኛ፡- የዲሲን መድኃኔ ዓለም ህዝብ ካዱ ከፈሉ።

፭ኛ፡- እውነተኛ መነኩሴ እንኳን ዜግነት መለዋወጥ በአቱን (በገዳም የሚኖርባት ጎጆ) አይለውጥም። እሳቸው ግን የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙ በኋላ ዜግነታቸውን ለወጡ። የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙ አይበቃምን? በትዳር ያለን ካህናት በቤተ ሰቦቻችን አማካይነት ከህዝብ ጋራ የምንጓተት በመሆናችን ዜግነትን መለወጥ የምንገደድባቸው ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ያም ቢሆን ለኔ ይከብደኛል።

፮ኛ፡- ከማህበረ ቅዱሳን ጋራ በማበር እምነቱን ከደው የተዋህዶውን እምነት "የመናፍቅ ነው" ብለው አወጁ። በስህተታቸውም ይሁን በክህደታቸው ደካማ ግንዛቤ ክህነትን አገዱ። ቤተ ክርስቲያናችን በነ አቶ ስብሀት እጅ ባትወድቅ ኖሮ፤ በተሳሳተ መንገድ እምነቱን ማውገዛቸው ክህነትም ማገዳቸው ከአቡንነት ብቻ አይደለም ለተከበሩ ዜጎች ምእመናን የሚሰጠው አቶነት የተነፈጋቸው መሆናቸው በታወጀባቸው ነበር።

፯ኛ፡- ከማህበረ ቅዱሳን ጋራ በመተባበር በዲሲ ማህበረ ካህናት ላይ ዘመቱ።

፰ኛ፡- በአቡነ ተክለ ሃይማኖት መወገዛቸውን እያወቁና አጻፋ ሲሰጡበት የነበረውን ውግዘት ከደው፤ ወያኔ አስቀድሞ ባፈረሳት ቤተ ክርስቲያናችን ፓትርያርክ ሆነው ገብተው እንዲያገለግሉት ያቀረበላቸውን ምልመላ ለመቀበል ስለፈለጉ አልተወገዘኩም ብለው ዋሹ።

፱ኛ፡- ያሜሪካን ዜግነት ትተው የጣሉትን ኢትዮጵያዊነትን ተላበሱ።

፲ኛ፡- አሁን ደግሞ በወያኔ ምሪት ለብዙ አመታት ይተባበሩት የነበረውን ማህበረ ቅዱሳንን ካዱ።

፲፩ኛ፡- በቨርጅንያ ኪዳነ ምህረት የተፈጸመውን ስህተት ምእመናኑ በበቂ ማስረጃ በቀረቡላቸው ጊዜ፤ " እንደቀላል የምንመለከተው አይደለም። በቅርብ ውሳኔ እንድታገኙ አደርጋለሁ" ብለው ቃል ከገቡ በኋላ የገቡትን ቃል አጠፉ። ለህዝበ ክርስቲያኑ ምንም ነገር ሳይናገሩ፤ በጥፋት የተከሰሰውንና በብዙ ህዝብ ተወግዞ ስህተቱ በቅዱሳት መጻህፍት ሚዛን ተፈትሾ ቅዱሳት መጻህፍት ያወገዙትን ግለ ሰብ ለመሸፈን በራሳቸው መዋቅር እንዲታቀፍና ቆሞስ እንዲሆን ፈቀዱ። በስራቸው ያለው የቤተ ክህነቱ ጋዜጣም፤ ግለ ሰቡን አስመልክቶ ለህዝብ ያቀረበው ዘገባ፤ በአዲስ ተክልነታቸው በተሳሳተ ግንዛቤ ያሰራጩትን ሀሳብ በማንጸባረቁ፤ ህዝበ ክርስቲያኑን በፓትርያርክነታቸው ላይ እምነት እንዲያጣና በቤተ ክርስቲያናችን ላይም የሚፈጸመውን ሴራ በግልጽ እንዲገነዘብ አድርጎታል። ይህም ሴራ ህዝቡን አንድነቱን አሰባስቦ ለእምነቱና ለቤተ ክርስቲያኑ የበለጠ እንዲቆም እያደረገው ነው። ከ፤ እስከ ፲፤ የተዘረዘሩትን ያቡነ ማትያስን ደካማ ጎኖች አጠቃለን ስንመለከታቸው፤ ወያኔዎች የጠነሰሱትን የኃጢአት የጥንስስ ገፈታ በአቡነ ጳውሎስ እንደጠጡት፤ አሁን ደግሞ ወያኔዎች የኃጢታቸውን አተላ የሚጋቱበት ዋንጫቸው ሆነው አቡነ ማትያስን መቅረባቸው ትልቅ ድካማቸው እንደሆነ እናገራለሁ። ይህ ካልሆነ፤ አቡነ ማትያስ ይህን ሁሉ ደባ በፈጸሙበት ህዝብ ላይ እንዴት ፓትርያርክ ይሆናሉ? ከዚህ በመቀጠል አባቶቻችን "እግዚአብሔር ያሳየዎ ክርስቶስ ያመልክተዎ" በሚሉት መርኋቸው ህሊናየን አንተርሼ ወደ ማሕበር ቅዱሳን እሻገራለሁ።

በራሳቸው ጥረት ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ በቅን መንፈስ የተነሳሱ ኦሮቶዶክሳውያን ዜጎች እንደሆኑም በሰፊው ይነገራል። እንደነ እስጢፋኖስ፤ እንደነ ቅዱስ ጊዮርጊስ እና ቂርቆስ የመሳሰሉ ምእመናን የተከሰቱት ሀሰት ክህደትና ሸፍጥ በበዙበት ዘመን ነው። በየዘመናቱም እነደ እነ ቅዱስ ጴጥሮስ የመሳሰሉ አመራር ላይ ነበሩ።

የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ስንመለከተው፤ ጥንታውያን ቅርሶች፤ ታሪኮችና ለሰባዊነት ታላቅ ክብር የነበራቸው ባህሎች በውስጥና በውጭ የሚከሰት ጠላት የሚደመስሳቸው ያልገባውንና መሰረት ያልተጣለበትን የሀገሪቱን ተወላጅ ወጣቶችን መሳሪያ በማድረግ ነው። ወያኔ አገራቸውንና ቤተ ክርስቲያናቸውን እያፈራረሰ በመጣበት ዘመን ማህበረ ቅዱሳን እንደተከሰተ ሁሉ እየተናገረው ነው። እነዚህ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች የተጠመቁባት ከወላጆቻቸው የተረከቧት ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያናቸውን ከውስጥና ከውጭ ለሚገጥማት ችግር መሳሪያ ከመሆን ይልቅ ቤተ ክርስቲያኒቱን ተከላክሎ ለማቆየት ያደረጉት ጥረት በእጅግ የሚደገፍ ነው።

ነገረ መለኮቱን እንደሆነ ከሊቃውንቱ በቀር እንኳን እነሱ ጳጳሳቱም አያውቁትም። ነገረ መለኮቱን ባለመረዳታቸው አይፈረድባቸውም። ማህበረ ቅዱሳን ናችሁ ተባሉ። ከስማቸው ጋራ የተሳሰሩትን ቅዱሳንን ብቻ መስበክ ጀመሩ። ሁሉ እንደነሱ እንዲሆንላቸው ፈለጉ። ይህም ስህተት ማህበሩን ሲመሰረቱ ፈቃድ በጠየቁ ጊዜ ሳያስተምር ሳያስረዳ ፈቃዱን የሰጠ የሚጠየቅበት ስህተት እንጅ እነሱ አይጠየቁበትም። ይልቁንስ ማህበረ ቅዱሳንን እንድንደግፈው የሚያስገድዱንን ነገሮች ከዚህ በታች እዘረዝራለሁ።

ሀ. አቡነ ማትያስም ሆኑ እኛ ካህናቱ ያላደረግነውን ከውጭ ከመጣ ድኖምኔሽንና ከወያን መሳሪያነት ራሳቸውን ጠብቀው፤ በየገጠሩ እየሄዱ አቅማቸው የፈቀደላቸውን ገዳማቱንና የገጠሩን አብያተ ክርስቲያናት አጠናክረዋል።

ለ. አቡነ ማትያስም ሆኑ እኛ ካህናቱ ያላደረግነውን ካንደኛ ደረጃ ጀምረው እስከ ኮሌጆች ድረስ በየትምህርት ቤቱ ባደረጉት ተጋድሎ፤ ብዙውን ወጣት ወደ ባእድ እምነት ከመበተን ታድገዋል።

ሐ. አቡነ ማትያስም ሆኑ እኛ ካህናቱ ያላደረግነውን በየቦታው ስለሚገደለው ህዝበ ክርስቲያን ድምጻቸውን አሰምተዋል። ስለሚቃጠሉት ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት ማንም ካህን፤ መነኩሴና ጳጳስ ትንፋሽ ሳያሰማ ተናግረዋል። ይህ የማይመቼው ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ድርጅታቸውን ከመበተንና በተናጠልም ከመጉዳት እንደማይመለስላቸው ግልጽ ነው።

መ. ሳያዳሉ፤ ሳይዋሹና በዘር በጎሳ በጥቅም ሳይደለሉ፤ በህዝብ መካከል ያሉ ጳጳሳትና ካህናት፤ ከገዳም ወጥተው በከተማ መኖር የጀመሩ መነኮሳት የሚያሳዩትን የሞራል ውድቀት በማስረጃ እየሰበሰቡ ለተመልካች ማቅረባቸው እና ሙዳየ ምጽዋት ገልባጮችን ማጋለጣቸው የሚደገፍና ቀጥሉበት እንዲባሉ የሚያደርጋቸው እንጅ ሚያስወቅሳቸውና የሚያስወነጅላቸ አይደለም።

## ፫ ኛ፦ የማህበረ ቅዱሳን አባላት በአገር ውስጥና በውጭ የፈጸሟቸው በጎና ከፉ ነገሮች

### በማህበረ ቅዱሳን ላይ ሙሉ በሙሉ ለመፍረድ አስቸራጊ ነገሮች።

ማህበረ ቅዱሳን የሰራውን ሁሉ በጎ ነገር እየደመሰሰበት ያለው በነገረ መለኮቱና በሊቃውንቱ ላይ የፈጸመው ዘመቻና፤ ቤተ ክርስቲያናችንን ከአቻወቿ እንድትለይ የሚያደርጋትን ስህተት መፈጸማቸው እንደሆነና፤ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ለአቡነ ጳውሎስ ሸፍጥም ሽፋን መሆናቸውም ነው።

ለምሳሌ፦ ከንሳስ ላይ በተከሰተው ስህተት፤ አቡነ ጳውሎስ በአኀት አብያተ ክርስቲያናት በተጠየቁ ጊዜ "የኮምኒስቱ መንግስት የሰየመው ባሚሪካ ያለው ያልተማረ ጳጳስ ከሰንበት ተማሪዎች ጋራ የፈጸመው ስህተት ነው። ያላንዳች ጥፋት አቡነ ቴዎፍሎስን በገደለበት እኔንም ባሰረበት ዘመን የኮምኒስቱ ስርአት ካወረሰን ከብዙ አስቸጋሪ ነገሮች አንዱ ነው። ስህተቱን ወደ ህዝቡ ከተው ስር የሰደ ስለሆነ ለማስተካከል ከመንግስት ጋራ እየተነጋገርኩበት ነው" ብለው በመናገር ከወቀሳና ከከሰሳ አምልጠዋል። ለአኀት አብያተ ክርስቲያናት ያቀረቡትን ይህን ዘዴ፤ ከአቶ መለሰ በቀር ለማንም ያካፈሉት አይመስለኝም። ነገሩ እየገፋ ሲሄድ ግን ባስተዳደርና በነገረ መለኮት እየገቡ አስቸገሩኝ ብለው ማህበረ ቅዱሳንን ባቶ መለሰ ዳኝነት ከሰሱ። አቶ መለሰም "አክራሪና አሸበሪ" የሚል ስም በማህበሩ ላይ ለጠፉበት። ይህም ከአኀት አብያተ ክርስቲያናትና ከከንሳስ ለሚወረወርባቸው ሸክም ፋታ እንዲያገኙ ረድቷቸዋል። በኋላ አቡነ ማትያስ አቡነ ጳውሎስን "ከፋፋይ ናቸው" ብለው የዘለፏቸው በዚህ ምክንያት እንጅ በመካከላቸው የራቀ ልዩነት አልነበረባቸውም።

ከተለያየ ጎሳ የተሰባሰበው የዋሁ ማህበረ ቅዱሳን ባልገባው ነገረ መለኮት ውስጥ ገብቶ ሲዘባርቅ፤ ከንሳስ ላይ በተከሰተው ነገረ ማርያም አባ ሠረቀን ከሶ ሲያቀርብ በተዘረጋበት ወጥመድ ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ። እኛ ካህናቱም ሆን ህዝበ ክርስቲያኑ በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ የሚደርሰውን ተንኮል መላ ምስራቃውያን ኦርቶዶክሶችና የዓለም አብያተ ክርስቲያንት ይልቁንም አኀት አብያተ ክርስቲያናት እንደ ሚከታተሉት ባንረዳውም፤ አቡነ ጳውሎስ ግን በሚገባ ስላጠኑት ያውቃሉ። ለፖለቲካው የሚሰጡት ድጋፍና ሽፋን እራሳቸውን ጠብቀው፤ በውጭ ተመልካች በማያስወቅሳቸው ዘዴ ነበር።

አስታውሱ! አባ ሠረቀን ለመታደግ ደብዳቤ እስከ ጳፉባት ቅጽበት ድረስ በአገር ውስጥ ለማንም ሳይናገሩ ማህበረ ቅዱሳንን እየደገፉ የእምነቱን መፋለስ እኛን ለመከፋፈል ሲጠቀሙበት ቆይተዋል። ታሪክ መናገር ሙት መውቀስ አይደለምና ለዚህ ሁሉ ጥፋት ተወቃሹ አቡነ ጳውሎስና አቶ መለሰ ናቸው። <u>ሁለቱ እየተነጋገሩ በፈጸሙት ደባ፤ አምላክ ሁለቱም እየተነጋገሩ ወደ መቃብር እንዲወርዱ አደረጋቸው።</u>

ሌላው ችግር የቤተ ክርስቲያናችን ይዘት ነው። ይዘቷ የሚያስቸግረው ሞራለ ቢስ መሪ ሲከሰት በሚፈጠረው ሁኔታ እንጅ ይዘቷ የሚያስነቅፋት አይደለም።

ብገልጸው የሚረዳ ይመስለኛልና ልግለጸው:- አንድ ዩንቨርሲቲ በቤተ መዛግብቱ የሚሰበስባቸው መጻህፍቶች ባንድ አይነት ሙያ ለሚያሰለጥናቸው ተማሪዎች ብቻና ለዚያ ሙያ የሚጥቅሙት መጻህፍት ብቻ አይደለም። ለሙያው ተቃራኒና ራቅ ያሉ ሀሳቦችን የያዙትን መጻህፍት ስብስቦ ቢገኝ ያስመሰግነዋል እንጅ አያስነቅፈውም። አንድ መምህር የኒቨርስቲው ስብስቦ ካስቀመጣቸው ከተለያዩ መጻህፍት እየቀራረመ ከሙያቸው ጋር የሚጋጭ በተማሪ ጭንቅላት ቢደፋ፤ መምህሩ ይነቀፋል ወይም ይባረራል እንጅ የንቨርስቲው መጻህፍቱን ሰብስቦ በመያዙ አይነቅፍም። እንደዚሁም የቤተ ክርስቲያናችን ግምጃ ቤት በነገረ እንግልጣር ከጻፉት ዘመናውያን መጻህፍት በቀር ሰብስቦ ያልያዘው የመጽሐፍ አይነት የለም። ስለ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ነገረ መለኮት ስናስተምር በማንረዳው ግእዝ ተጽፈው በእቃ ግምጃ ቤት ካሉት መጻህፍት እየቀራረምንና በየመንደሩ የሰማነውን እያግበሰበሰብን ለምእመናን ማሸከም ስህተቱ የተናጋሪው እንጅ የቤተ ክርስቲያናችን አይደለም።

ቤተ ክርስቲያናችን ሰብስባ የያዘቻቸውን መጻህፍት። በየገጻቸው ለይቶ መረዳት የሚቻለው በቅኔው ትምህርት በስሎ። መጻህፍትን በማመስጠር ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ነው። በምንኩስና በጵጵስናና በቁምስና ንክኪ እንደልብሱ የሚጠለቅ ነገር አይደለም። ሐላፊነቱን የወሰዱት አባ ጳውሎስ ከነአቶ መለሰ ጋራ እየተነጋገሩ ማህበረ ቅዱሳንንንም ከነገረ መለኮቱና ከሊቃውንቱ ጋራ በሚጋጭበት እንዲቀጥል እያበረታቱ የሊቃውንቱን ሞራል እየሙቱ፤ የተፈጸመ ስህተት ስለሆነ፤ ነቅተን በመነሳት የሚታረመውን እያረምን የሚገሰጸውን እየገሰጽን ወደፊት ከመሄድ በቀር፤ አሁን ከወያኔ ጋራ ተባብሮ በማህበረ ቅዱሳን ልጆች ላይ መዝመት የበለጠ ጉዳት ይመስለኛል።

### *ሀ.* <u>*ማህበረ ቅዱሳን በአገር ውስጥ*</u>

ሃይማኖተ አበው የተባለውን ታሪካዊ ድርጅት ከማፍረሳቸው ባሻገር፤ ከውስጥ ከሚመጡት ካህናት እንደ ሰማሁት እንደ የኔታ ያሬድ፤ በኋላ አቡነ መርሐ ክርስቶስን በተባሉት አባት ላይ ሳይቀር እንደዘመቱባቸው በሰፊው ተነግሯል። ዛሬ በዘመናችን "ቆሞስ ማለት ጳጳስ ሊሆን ትንሽ የቀረው" እየተባለ በሚሰበክበትና፤ ሲኖዶስ የሚባለውም ከሜዳ እየተሰበሰቡ ለእምነቱ አዳዲስ ተክሎች የተሰገሰጉበት ስለሆነ፤ ማንም ጳጳስ ሊሆን ይችላል። ማንም ግን እንደ የኔታ ያሬድ (አቡነ መርሐ ክርስቶስ) የሙያ ሰው ሊሆን አይችልም።

ማህበረ ቅዱሳኖች በሰፊው የሚወቀሱበት በገንዘብና ረብ በሌለው ጥቅም ከመካከለቸው እየመለመሉ ካስገቧቸውና አባ ጳውሎስም ለፖለቲካቸው ሲሉ ከሰገሰጓቸው ሰዎች ጋራ፤ እንደነ የኔታ ያሬድ (አቡነ መርሐክርስቶስ) እና መጋቤ ብሉይ ሰይፈን የመሳሰሉትን ሊቃውንትን እኩል በመመልከት ማሳዘን ቤተ ክርስቲያናችንን መጉዳት ነው። ድሮም ቢሆን ባይማርም ማንም መነኩሴ መንፈሳዊነቱ ትህትናው ግብረ ገብነቱ ለጳጳስና ያቀርበዋል። በትምህርት ዘልቆ አለመራመዱ ከጵጵስና አያርቀውም። ማንም ግን እንደነ የኔታ ያሬድና መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሊሆንና እነሱን ሊተካ አይችልም። <u>አንደነሱ ያለትን ሊቃውንት ሞራል ለመምታት መሞከር፤ ቤተ ክርስቲያኒቱን ጨርሶ መግደል ነው። እንደነሱ ያሉትን ከማጣት፤ በዕውቀትና በሞራል ድህነት የተራቆቱት ግለ ሰቦች የተሰበሰቡበትን ሲኖዶሱን መበተን እጅግ ይቀላል።</u>

ሁሉም እንደሚያስታውሰው፤ ነፍሳቸውን ይማርና የሊቃውንት ጉባዔ መሪ የነበሩት መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ለእርቅ በተጀመረው ድርድር በንቡረ እድ ኤልያስ መሪነት ወደ አሜሪካ ከመጡት ልኡካን ጋራ የሊቃውንቱን ጉባዔ ወክለው ወደ አሜሪካ መጥተው ነበር። በዚያ ዘመን ፍልሰታ ቀዳሚት ስለተጀመረች ሐሙስ የፍልሰታ ጾም ቅበላ ነበር። የቀበላውን እራት ያዘጋጁት

የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንን እወክላለሁ ይሉ የነበሩት አባ አብርሃም የሚባሉት ነበሩ። እሳቸው ባዘጋጁት እራት ላይ ካንድ ወዳጄ ጋራ ተገኝቼ ነበር። የተገኘሁበት ምክንያት እስከዚያ አመት ድረስ የጻፍኳቸውን ጦማሮች በዲስክ ሰብቤ እንዳቀብላቸው በመጋቤ ብሉይ ተጠይቄ ለማቀበል እንጅ ለራቱ አልነበረም።

አባ አብርሃምንም ያወኳቸውና ያስተዋወቁኝ በራቱ ግብዣ ላይ መጋቤ ብሉይ ሰይፈ ነበሩ። በአቡነ ገሪማና በመጋቤ ሰይፈ ጎን ተቀምጬ ነበር። አቡነ ገሪማ "አንተ የውጬ ኑሮ አይሰለችህም? ለምን ወደ አገርህ አትገባም? ብለው ጠየቁኝ። እኔ በነበርኩበት ዘመን የነበሩትን ሰዎች ጠቃቅሼ እነሱ ሁሉ ሞተዋል። ማን ያውቀኛል ብየ እመለሳለሁ? ስላቸው፤ "እኛ አለን። መጋቤ ብሉይ ሰይፈም አለ። ለምን እንዲህ ትላለህ? አሉኝ። የመለስኩትን ከመለስኩ በኋላ፤ ሰይፈ ቀጠሉና "ለአንተ የገጠመህ እድል ለማንም አልገጠመውም። በያዝከው ቀጥል። ባሁኑ ወቅት ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰህ ግባ ብየ አልመክርህም" ካሉኝ በኋላ፤ የማህበረ ቅዱሳን አባላት ከአቡነ ጳውሎስ ጋራ በመተባበር በሳቸውም ላይና በሌሎች ሊቃውንት አበው ላይ የፈጸሙትን ዘመቻ፤ ከዚህ በታች የገለጽኩትን ነገሩውኛል።

"ቢያንስ በቀን አምስት ስድስት ሰዎች ማህበረ ቅዱሳን ከሚባለው ድርጅት ወደ ቢሮየ እየመጡ፤ <አንተ መናፍቅ ተነስ ከዚህ ይሉኛል> ከቤተ ክህነት ውስጥ ያለን ሰዎች ጭንቀት ብቻ እንጅ የመንፈስ እረፍት የለንም"። በነጻው አገር ላይ በምትኖረው በራስህ ላይ የሚያደርጉትን አታየውም? በእመቤታችን ስም ቁራሽ እየለመንክ ተምረህ ያደከ መሆንህን ሁሉም ያውቃሉ። እስቲ ገምተው! ከአቡነ ማትያስ ጋር በትምህርት ገበታ ባትተዋወቁም፤ በቤተ ክህነቱ ግቢ ባንድ ቤት አብራችሁ በመኖር የሚያውቁህ አንተን ነው። አቡነ ማትያስን ባልደከሙበትና በማያውቁት ነገረ መለኮት ገብተው፤ ከማህበረ ቅዱሳን ጋራ በማበር ማርያምን ስለ ካደ አግጃለሁ የሚል ወረቀት ወደኛ መላክ፤ ባልተማረውና ባሉባልታ በሚነጉደው ህዝብ ለማስጠላት መሞከራቸውን እራስህ እንዴት ትረዳዋለህ? ይህም ብቻ አይደለም መኪናህንም ሳይቀር እንደሰበሩብህ ሰምተናል። ምን አደረካቸው ? ምን በደልካቸው ?

"አሜሪካ ሆነህ ያላንዳች ምክንያት ይህን ግፍ ከፈጸሙብህ፤ እውስጥ ባለነውማ ምን ያህል መከራና ግፍ እንደሚፈጽሙብን መገመት ትችላለህ" አሉኝ። "አቡነ ጳውሎስ ተው አይሏቸውም?" ብየ ለጠየኳቸው የሰጡኝ መልስ የትካዜ ፈገግታ ነበር። በዚያው ምሽት ከእራት በኋላ ቆመው "ውቅያኖስ አቋርጠን የመጣንለት ሰላም ሳይሳካ የእግሬን ትቢያ አራግፌ ይህችን መሬት መልቀቄ እጅግ አሳዝኖኛል" ብለው ባቀረቡት ንግግር የሐሙሱን ምሽት አሳልፈን በመሰነባበት ተለያየን። ቅዳሜ ከኢትዮጵያ ለመድረስ ዓርብ በጧት አሜሪካን ለቀቁ። እኔም ቅዳሜ ከዲሲ ወደ ከንሳስ በመመለስ ከአየር ወርጄ ወደ ቤቴ ለመድረስ በመኪና ውስጥ ሳለሁ፤ ዲሲ የሚኖር ወዳጄ "መጋቤ ብሉይ ከአየር ወርደው እግራቸው የኢትዮጵያን መሬት ሲነካ ሞቱ" ብሎ በስልክ አረዳኝ።

መርዶውን ስሰማ ራሳቸው መጋቤ ብሉይ ከነገሩኝ በመነሳት፤ ከደረሰባቸው መከራና ጭነት ጋራ ደምሬ የአሟሟታቸውን ሁኔታ ሳስበው፤ ከልጆቻቸውና ከሚያፍቅሯቸው ወገኖቻቸው ባልታሰበ ቅጽበት መለየታቸው ቢያሳዝነኝም፤ የማህበረ ቅዱሳን ሰዎች በየቀኑ ወደ ቢሯቸው በመሄድ የሚወረወሩባቸው ዘለፋና ጥላቻ ለህልፈታቸው ምክንያቶች አንዱ ይሆናል ብየ እንዳስብ አድርጎኛል።

## ለ. <u>በአሜሪካ የታዩባቸው ከፉ ጎኖቻቸው</u>

አበ ሡረቀ "ንጋትና እውነት" በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሀፍ፤ በገጽ 29 እና 38 ላይ የሰፈረው ዘገባ ከፈለኝ ወልደ ጊዮርጊስ በሚባለው የማህበረ ቅዱሳን መሪነኝ የሚለው ግለ ሰብ ያዘጋጀው የካህናቱ ቃለ ጉባዔ ነበር። የካህናቱ ጉባዔው አቡነ ማትያስ ስህተታቸውን እንዲያስተካክሉ የጠየቋቸው፦ 1ኛ፦ አቡነ ግብርኤል 2ኛ፦መጋቤ አዕላፍ መክብብ 3ኛ፦ ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህን በመላክ ነበር። ይህ ከፈለኝ የሚባለው የማህበረ ቅዱሳን መሪ ከነሱ ጋራ ሄዶ አቡነ ማትያስ የተናገሩትን ከመዘገበ በኋላና፤ ከማህበረ ካህናቱ ጋራም ሆኖ የአቡነ ማትያስን አቋም የሚጻረረውን የካህናቱን ቃለ ጉባዔ ራሱ መዝግቦ አብሮ ፈርሞ ወደ አባ ጳውሎስ ከላከ በኋላ፤ እንደገና ተገልብጦ ከዳንዔል ክብረት ጋራ ወደ አቡነ ማትያስ በጎድን ሄዶ፤ ከገጽ 34 እስከ ገጽ 45 ድረስ ያለውን የካህናቱን ቃለ ጉባዔ የሚጻረረውን ጽፎ አቡነ ማትያስን አስፈርሞ ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ላከው። ባሜሪካ ዙሪያ ላሉ ምእመናንም በተነው።

ቆይቶ ደግሞ "ከካህናቱ ጋራ ተባብሬ ሃይማኖቴን ክጄ ነበር። የካህናቱ እምነትና ትምህርት ስህተት ሆኖ ስለተረዳሁት ከክህደቴ ተመለስኩ" የሚል ነገር አሐቲ ተዋህዶ በሚባለው ድረ ገጽ ላይ በመለጠፉ ብዙ ሰው አሳዘነ። በማህበረ ቅዱሳን ስም በዚህ መንገድ የሚያተራምሱ ሰዎች ፤ በማህበሩ ላይ ያተረፉትን ጥላቻ መገመት የሚከብድ አይደለም። አሁን ደግሞ ይህ ግለ ሰብ በተለያዩ እስቴቶች ሲዘዋወር ከቆየ በኋላ ማርያምና ገብርኤል በሚል ስም በዲሲ ዙሪያ ቤተ ክርስቲያን መክፈቱን ሰማሁ። ይህን በመሳሰሉ ሰዎች በቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስም የሚከፈቱት አብያተ ክርስቲያናት ተልእኳቸውን መገመት ቀላል ነው። እነዚህ ሰዎች ይህን ሁሉ ትርምስ የሚፈጥሩት እውነት ለቤተ ክርስቲያን አስበው ነው ማለት ይቻላልን?

ለሊቃውንቱ ይሰጥ የነበረው ሊቀ ኅሩያን የሚባለውን የማእረግ ስም፤ በስሙ ላይ ለጥፎ እየተጠራበት ነው። በዚህ ስም ማን ሰየመው? ቅስናውንስ ማነው የሰጠው? ቤተ ክርስቲያንስ ክፈት ብሎ የፈቀደለትስ ማነው ? ለዚህ ግለሰብ ቅስና፤ ቤተ ክርስቲያን ክፈት ብሎ ፈቃድ የሰጠና ሊቀ ኅሩያንም ብሎ የሰየመ ግለ ሰብ ተጠያቂ ነው።

ሰወች ተመልከቱ! ቀድሞ የሰው ቁጥር ባልበዛበት አሳቹ ሰይጣን ወደ ሰው የመጣው በእባብ ነው። አሁን ግን እነዚህን በመሳሰሉ ሊቀ ኅሩያኖች፤ መላከ እገሌዎች። ርእሰ ደብሮች፤ በመነኩሴዎች፤ በቄሶችና ባስመሳይ ሰባኪዎች ተሰውሮ ነው። ይህን ሁሉ ሲፈጽሙም ብቻቸውን አይደለም። “ጳጳስ ለመሆን ትንሽ የቀረኝ ቆሞስ ነኝ” እያሉ ሲያወናብዱ ኖረው፤ በኋላ ወደ ጵጵስናው በመጡ ሰዎች እየታጀቡ ነው። ታዲያ የነዚህ ሰዎች መሰረት የሌለውን ምእመናን ሁሉ ወደ ሌላ እምነት መሾኘት ይቅርና፤ ጭራሽ ክርስትናን አያስክድምን? በጳጳሳቱ የታየው የሞራል ውድቀት የቀነሰውን ያህል የምመናን ቁጥር መጠን ባይመጥንም፤ በማህበረ ቅዱሳን ተሸፍነው እነ ከፈለኝ የፈጸሙት ደባ የምእመናን ቁጥር አይቀንስም ማለት ይቻላልን?

## ፯ ኛ፡- መደምደሚያ

“ይህን የቄሱን ቃል የናቀና ያቃለለ ይወገድ” የሚለው የቤተ ክርስቲያናችን አዋጅ፤ በወያኔ መርሆ ላይ ተደግፈው አቡነ ማትያስ ስለሚናገሩት ቃል አይደለም። ወያኔን በመሰለ ቡድን እየተደገፈና ከወያኔ ትዕዛዝ እየተቀበለ ወደ ህዝብ የሚወረወረውን ቃል መቀበል ቀርቶ፤ ራሱ ተናጋሪው መወገድ አለበት። አለበለዚያማ ቅስና ለውሸት ለማስመሰልና ለማታለል ፈቃድ መሆኑ ነውና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ነገረ መለኮት አይቀበለውም። ክህነት የሌላቸው የዘመኑን ትምህርት ተምረናል የሚሉት ምእመናንም፤ የመምህራን ምሳሌና የእውቀታቸው ምንጭ የሆነው “ለውነት እሞታለሁ” ብሎ ሶቅራጥስ የተናገረው አይቀበለውም። ተማርኩ የሚል ቡድን ከሶቅራጥስ መርሆ ከራቀ፤ ካህናትና ክርስቲያኖችም ከክርስቶስ መርሆ ከራቁ፤ የሚኖሩባት አገር ከወደቀችበት አዘቅት መውጫ አይኖራትም።

”እግዚአብሄር ያሳየዎ ክርስቶስ ያመልከተዎ! የሚለው ኢትዮጵያዊ ባህላችን እንደ ሰሎሞን ሰይፍን በመጠቀም ቤተ ክርስቲያንን ተጭኖ እየገደላት ያለውን አካል ለይተን እንድናውቅበት የደረሰንበት ይህ ዘመን ይማጸናል። አቡነ ማትያስ በማህበረ ቅዱሳን ላይ ያቀረቡት የወቀሳ ክስ ጨርሰን ሳንጥል፤ ማህበረ ቅዱሳኖችም በኛ በካህናቱ ላይ የሙዳየ ምጽዋት ገልባጮች? ዝሙተኞች ጳጳሳት መነኮሳት፤ ዘመኑ የፈለፈላቸው ቆሞሳት፤ ቀሳውስት ላይ ያቀረቡብንን ክስና ወቀሳ ሳንሸፍን፤ እግዚአብሔር በሚያሳየን ክርስቶስ ባማለከተን ቀስት መመርመር አለብን።

አቡነ ማትያስ እውነት ለቤተ ክርስቲያን ከተቆረቆሩ፤ እነ አቶ ስብሀት ነጋ እራሳቸውን በመለመሉበት መንገድ ለቤተ ክርስቲያን መሪ ሆኖ ቢገባ ምቱር ነውና እንዳትቀበሉት የሚለውን መመሪያችን ለምን ጥሰው ገቡ? ከገቡስ በኋላ ማህበረ ቅዱሳኖች ስለ ገዳማት መደፈር፤ ስለ ህዝበ ክርስቲያኖች መገደል፤ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎች መቃጠል የተናገሩት፤ በየጠረፉ ስላሉት ዜጎቻችን መንገላታት እንድናለቅስና ወደ ፈጣሪያችን እንድናቀርበው የነገሩንና ያረዱን ማህበረ ቅዱሳን አባላት ናቸው። ምንም ማድረግ ባንችልም እርም ከመብላት ስላዳኑን እናመሰግናቸዋልን።

አቡነ ማትያስ ማህበረ ቅዱሳን በሰበሰበው በገንዘቡ ላይ ከመዝመታቸው በፊት፤ “ጳጳሳት ወለዱ፤ ንብረት በማፍራት ቤት መስራት ተሰማሩ፤ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ማወቅ ቀርቶ ህጻናት ሆነን በቃላቸን በመያዝ ያፋችን መፍቻ የነበረውን ውዳሴ ማርያም እንኳ የሰሙ አይደሉም፤ ከየሰፈራቸው ይዘውት በገቡት ተረት ቤተ ክርስቲያኒቱን እያሽከረከሯት ነው” እየተባለ ለብዙ አመታት ሲነገር ቆይቷል። ለምን ይህን ተራመዱት? በለንደን፤ በአሜሪካና በሌሎች ቦታዎች ሁሉ የሚታየውን ቀውስ፤ እንደ ሌሎች ፓትርያርኮች በህዝቡ መካከል እየተገኙ ችግሩን ለማስተካከል ለምን አልሞከሩም? በማህበረ ቅዱሳን ላይ ካቀረቡት ክስ ይልቅ ጳጳሳቱና ቆሞሳቱ የሚፈጽሙት በደል አይከፋምን?

ሙዳየ ምጺቱን ህዝብ ለሚገለው ለወያኔ ሰጡ ተብለው ሲወቀሱ የቆዩት እራሳቸው ናቸው። የህዝቡን ገንዘብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ዘረፉት ሰረቁት እየተባለ በግልጽ ሲነገር የሚሰማው በጳጳሳቱ በቆሞሳቱና በካህናቱ ላይ ነው። ለገዳማት ላብነት ትምህርትና ለፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት ሰጡ እየተባለ እንጅ፤ ማህበረ ቅዱሳኖች ለወያኔ ሰጡ ተብለው ሲወቀሱ አልተሰማም። ራሳቸው አቡነ ማትያስም ማህበረ ቅዱሳን ”የሚሰጣችሁ ከናንተ የሰበሰበውን ገንዘብ ነው” እያሉ በተናገሩት፤ ማህበረ ቅዱሳን ገንዘብ ቢሰበስብም ለህዝቡ እንደሰጠው መስክረዋል። እንኳን ማህበረ ቅዱሳን፤ ያሜሪካ መንግሥት ለህዝብ መልሶ የሚሰጠው ከህዝብ የሰበሰበውን ነው። ለህዝብ መልሰው መስጠታቸው እንዴት ሊያስወቅሳቸው ይችላል?። ይህ አቡነ ማትያስ በማህበረ ቅዱሳን ላይ ያቀረቡት ክስ፤ ማህበረ ቅዱሳንን “አያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ” የሚያሰኘው ይመስለኛል።

እውነት ከቤተ ክርስቲያን እየተሰበሰበ ከዓረብ አገር ለተመለሱት ከተሰጠና ከተረዱ የውጩ አሞራ ይብላን ብሎ ወደ ዓረብ አገር ለምን ተመለሱ? ከወያኔ ጋራ ተሰልፎ ቅልጥሙን እየመጠጠ ጮማውን እየቆረጠ ሊፈርጥ የደረሰውን ቆሞስ፤ ከዓረብ አገር ለተመለሰው ህዝብ "ወደ ስደት እንዳይመለስ አስተምሩ" የሚሉት ማበድ አይደለምን? እሳቸውስ ቢሆኑ ሌሎች ፓትርያርኮች እንዳደረጉት፤ ከዓረብ አገር የተመለሱትና በየቦታው በመበታተን ላይ ባለ ህዝብ መካከል ተገኝተው የወደቀበትና ቦታና ምን እንደሚቀምስ ለማየት አንድ ቀን እንኳ ሄደው ጎብኝተውት ያውቃሉ? ታዲያ ይህ አነጋገራቸው ወያኔን ሊጋስ ቸርና ታዳጊ። ህዝቡን በርጋጊና አገር የማይወድ አድረገው እየከሰሱ አይደሉምን?

እስካንሁ ያቀርብኳቸው የአቡነ ማትያስ ድካምና ጥፋት ወያኔ ***"የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጭ ግንባር በ1979 አመተ ምህረት አስተሳሰብ ለዋጭ የፕሮፓጋንዳ መርህ ግብር ለሚመለምላቸው ቀሳውስት ዘረጋ። የማሰልጠኑ ዓላማ ቤተ ክርስቲያኗን ከህዝብ ለይቶ በመምታት ስፋቷን ማጥበብና በትግሬአዊነት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስሜት በትግራይ ተወላጆች ጭንቅላት መክተት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ራሷን ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው።"***

ብሎ ገና ከመጀመሪያ ያቀደውን የጥፋት እቅድ በአገር በቤተ ክርስቲያንና በጠቅላላው ዜጋ ላይ ለማስፈጽም ታጥቀውና ተዘጋጅተው የመጡ መሆናቸውን አያሳይምን? ለመሆኑ በነጋ በጠባ ሲያወግዙት የነበረው ደርግ ወያኔ ከፈጸመው ግፍና በደል የከፋ ነበርን? በወያኔ የሚገደለው ህዝብ ያበደ ውሻ ነውን? ይህስ ዘረኛነታቸውንና ፖለቲከኛቸውን እየመሰከረባቸው አይደለምን? "ለእመ ሀልቀ ሰብእ ሡዑ ሰብአ" ከሚለው ከአሚነአረሚ፤ ማለትም <u>እንስሳ ከጣህ ሰው ሰዋ</u>" ከሚለው ከአረመኔ ሃይማኖት ላይ አልወደቅንምን? "እግዚአብሔር ባሳየን ክርስቶስ ባመለከተን እንድንፈርድ ይረዳን ዘንድ ይህችን ጦማር ለመላ ህዝበ ክርስቲያን አቀርባለሁ።

ይቆየን